<u>ሰወች እንዳትፈሩ</u>

እምነት እስተዳር

ፍርርሙ ሲፈርስ፣
ቃል ኪዳኑ ሲጣስ፣
ውሉ ሲልከሰከስ፣
ቋጠሮው ሲበጠስ፣
ስልፉ ሲተራመስ፣
ሰዎች እንዳትፈሩ ፈሪ ቤት አይሰራም፣
ፍሬም አያፈራም፣
አገር አያቀናም።

ብስሉ ሲለዝዝ ስጡ ሲወረዛ፣
ያመኑበት ብርቱ ለሆዱ ሲገዛ፣
ስንቁ እንከን ሲይዘው ብልጦቹ ሲነቅዙ፣
መድሃኒት ባሉት - መርዝ ሲመረዙ፣
ዳርና መሃሉ ሲጨመላለቁ፣
ስልፉን ሳይጠብቁ፣
ሲደበላለቁ፣
ልጓሙ ሲበጠስ እርፉ እጅ ሲበላ፣
ቁስሉ ሲመረቅዝ ጥብቁ ሲላላ፣
ጅንፎ ሲገባበት የታጀለው ዱላ፣
ሰወች ልብ በሉ እንዳትፈሩ ሆላ።

መረር በሉ ሰዎች የከፋው ቢከፋ፣
ለጊዜ ተሰግዶ አይጣልም ተስፋ።
የተሰበሩትን በወጌሻ አሽታችሁ፣
ለሞቱ እንባችሁን በብዙ አፍስሳችሁ፣
ለታሰሩ ስንቁን በውቀቱ አድርሳችሁ፣
የርስ በርስ ትዝዝን አይዞን ሆኖ ትጥቁ፣
በርቱ ተባብላችሁ ይህን ወቅት ዝለቁ።

በሰሞነኛ ግፍ እየተነጠቁ፣
ልጆቻችሁ አድገው ለፍሬ ካልበቁ፣
ከበራፋችሁ ላይ እሳት እየጤሰ፣
አየሩ ተለክፎ መርዝ ካስነጠሰ፣
የጅል ጉልበተኛ አጋፋሪ ሆኖ ህዝብ ካስለቀሰ፣
አገሩ ለዛውን የደስ ደሱን ሲያጣ፣
ሹማባሽ፣ ቡልቅባሹ፣ ካፈር እስኪገባ (ካገር እስኪወጣ)
ድፍር፣ ጭክን፣ ብርትት፣
ቆፍጠን፣  አሞት ክትት፣
አፈፍ፣ ያዝ፣ ጥንክር፣
እንቅ መርሆውን፣ የትግሉን መፈክር

ጠበቅ አላማውን፣ ጨበጥ ሰንደቁን
ጀግኖች ልጆቻችን የተሰውለትን፣
የታሰሩለትን፣ ኢትዮጵያዊነትን።

ጉብዝና ስትሸጥ ወጥታ በጨረታ፣
ፀሀይ ስታለቅስ ጨረቃን ሸኝታ፣
ምድር ስትተክዝ ግፋቸውን አይታ፣
ከመደፈር በላይ እንዳትደፈሩ፣
ነግሬለሁ ሆላ ሰወች እንዳትፈሩ።
ፍርሃት ባለጌ ነው የእንፋቅቅ ያስኬዳል፣
ሃሞትን ያፈሳል፣ ጉልበት ያሳቅፋል፣
ወገንን ለቀን ጅብ አሻግሮ ያሰጣል።

ጠቆሚ አስጠቆሚው አሳሪ ገራፊ፣
አቶንቶኝ ከሃዲው ንጅስት ተላካፊ፣
ጠላፊ አቃጣሪ ታጣፊ አሳላፊ፣
ሊሞት የደረሰ ፈሪ ሲንፈራፈር፣
ጠበቅ ይበል ወኔ ልብ እንዳይሸበር።
ፍርሃት አጥር ነው እስ በስ ያሻሽጣል፣
በደም አይመለስ አገር ያስፈርሳል።

Este_dar@yahoo.com